# ሁሉም ክርስቲያኖች ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ ተጠርተዋል

እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው *ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው*፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ። ማቴዎስ ወንጌል 28:19

***ደቀ መዝሙር የመሆን አላማው በዚህ ህይወት ልክ እንደ ኢየሱስ መሆን ነው***

ደቀ መዝሙር ከመምህሩ አይበልጥም፤ ፈጽሞ የተማረ ሁሉ ግን *እንደ መምህሩ ይሆናል*። ሉቃስ ወንጌል 6:40

***ደቀ መዛሙርት መሆን የምንችለው እንዴት ነው ?***

**1. <u>*መጽሐፍ ቅዱስን ዕለት ዕለት (በየቀኑ) አንብቡ።*</u>**

እርሱም መልሶ። ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው። ማቴዎስ ወንጌል 4:4

**2. <u>*የእግዚአብሔርን ቃል ታዘዙ*</u>**

እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደ ጠበቅሁ በፍቅሩም እንደምኖር፥ ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ። ዮሐንስ ወንጌል 15:10

በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል። ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከበራል። ዮሐንስ ወንጌል 15:7-8

**3. <u>*የየቀኑን የመጀመሪያ ሰዓት ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት አሳልፉ*</u>**

አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል። ማቴዎስ ወንጌል 6:33

**የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና**፥ የሚፈልግም ያገኛል፥ መዝጊያውንም ለሚያንኳኳው ይከፈትለታል። ሉቃስ ወንጌል 11:10

እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ። ዮሐንስ ወንጌል 16:24

**4. <u>*በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔርን በታማኝነት አገልግሉ።*</u>**

"ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤ ከእርሱም የተነሣ *አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ*፥ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፥ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።" ኤፌሶን 4:15-16

**5. <u>*ብርሃናችሁን በዓለም (ሥራ፣ ትምህርት እና ጨዋታ) ውስጥ አብሩ።*</u>**

መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ። ማቴዎስ ወንጌል 5:16

**6. <u>*የህይወታችሁን ዓላማ ጌታ ኢየሱስን ለማወቅና ከእርሱ ጋር ለመራመድ (አካሄዳችሁን ከእርሱ ጋር ለማድረግ) አድርጉ።* Make your life Goal to know the Lord Jesus and to walk with Him</u>.**

የመለኮቱ ኃይል፥ በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ፥ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን፥ በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ እውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ። 2ኛ ጴጥሮስ 1:2

http://www.shekinahworship.com , http://free.messianicbible.com/ , http://www.levitt.tv/ , http://www.choothomas.org , http://www.tribulation-now.org, http://www.thelordshour.com